# የኢትዮጵያ የፎቶ አርካይቭ ሕትመት

ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ
ክምችት ክፍል ተወስዶ የተዘጋጀ



**4ኛ ሕትመት**

ግንቦት 2009
አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ

# የኤጀንሲው ዓላማ፣ ተልዕኮ ፣ ራዕይ እና የጋራ እሴቶች እና መርሆች

## ዓላማ

- የሀገሪቱን የመረጃ ሀብቶች በማሰባሰብ፣ በማደራጀት፣በመንከባከብና በመጠበቅ ለጥናትና ምርምር እንዲሁም ለማገናዘቢያ/ሪፈረንስ/ አገልግሎት ማዋል፡፡

## ተልዕኮ

- የሪከርድ ስራ አመራር እና የመረጃ ስርዓት በመዘርጋት መዛግብትን፣ የጽሁፍ ቅርሶችን፣ እና የታተሙና ያልታተሙ የመረጃ ውጤቶችን በማሰባሰብ፣በማደራጀት፣ በመጠበቅ፣ ተደራሽ በማድረግና የጥናትና ምርምር ስራን በማሳደግ ለትውልድ ማስተላለፍ እንዲሁም የዕውቀትና የክህሎት ማሳደጊያ የልዕቀት ማዕከል በመሆን በዕውቀት የበለጸገ ማህበረሰብ መፍጠር

## ራዕይ

- በ2017 በመዛግብት፣ በጽሁፍ ቅርሶች፣ በታተሙና ባልታተሙ የመረጃ ውጤቶች ከምችት አደረጃጀት፣ አገልግሎት አሰጣጥና ተደራሽት በአፍሪካ በመጀመሪያ ደረጃ ካሉት አምስት ብሔራዊ አቢያተመዛግብትና አቢያተ መጻሕፍት አንዱ ማድረግ፡፡

## የጋራ እሴቶችና መርሆች

- ለሙያዊ ስነ ምግባር መገዛት
- ብቁና ቀልጣፋ አገልግሎት
- አሳታፊ አመራር
- ተጠያቂነት
- ግልጸኝነት
- ለለውጥ ዝግጁነት




**አድራሻ**

ስልክ፡- 251 0115 150882
ፋክስ፡- 251 0115 526411
የመ.ሣ.ቁ፡- 717
ኢ-ሜይል፡- nala@nala.gov.et
ዌብ ሳይት፡- www.nala.gov.et

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ አብይ ተልዕኮ የሪከርድ ስራ አመራር በማዘመን እና ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የመዛግብት፣ የጽሑፍ ቅርሶች፣ ያልታተሙና የታተሙ የመረጃ ውጤቶች በማሰባሰብ ፣ በማደራጀት እንዲሁም ጠብቆ በማቆየት ለህብረተሰቡ ተደራሽ በማድረግ ለጥናትና ምርምር እንዲበቁ በማስቻል ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፉ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በቤተመጻሕፍት እና በሪከርድ ስራ አመራር ሙያ ስልጠና በመስጠት በዕውቀትና በክህሎት የጎለበተ ህብረተሰብ በመገንባት ሀላፊነቱን በመወጣት ላይ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡ በመሆኑም ተቋሙ ከሰባ አመታት በላይ ለደንበኞቹና ለበርካታ አንባቢያን ፣ ለተመራማሪዎች፣ ለደራሲያን፣ ለጋዜጠኞች ዘርፈ ብዙ የመረጃ ሀብቶችን በማቅረብ አገልግሎቱን በመስጠት በሀገራችን ዋነኛ የዕውቀት ምንጭ በመሆን በመረጃ የዳበረ ህብረተሰብ ለመፍጠር የራሱን ሚና በመጫወት ላይ ይገኛል፡፡ ኤጀንሲው በስሩ የሚገኙ የመረጃ ሀብቶችን ለሌሎች ተቋማትና ለዜጐች ከማስተዋወቅም በጎን የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ትኩረት በማድረግ ሕዝበ ገለፃዎችን ፣ ሴሚናሮችን፣ አውደ ርዕዮች በማዘጋጀት በሀገራችን የንባብ ልምድ እንዲያድግ ጥረት እያደረገ ነው፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ሀገራዊ ሰነዶችን/መዛግብቶችን/፣ ፎቶግራፎችን፣ ካርታዎችን፣ የድንበር ስምምነቶችን፣ የህትመት ውጤቶችን (መጽሐፍት፣ መጽሔት፣ ጋዜጦችና የመሳሰሉትን)፣ ፖስተሮችን፣ የሠርግ ጥሪ ወረቀቶችን፣ የ40 ቀን መታሰቢያ ካርዶችንና የመሳሰሉትን በማከማቸትና ጠብቆ በማቆየት ለአገልግሎት እያዋለ ይገኛል፡፡ በዚህ ህትመትም የተዘጋጁ ፎቶግራፎች የኤጀንሲው ተግባር አንዱ መገለጫ ነው፡፡ በኤጀንሲዉ የአርካይቭ ክምችት ውስጥ ከ 3000 በላይ የፎቶግራፍ ክምችቶች ይገኛሉ፡፡ የፎቶግራፍ ክምችቶች ዘርፈ ብዙ የሆኑ ኢኪኖሚያዊ ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች እንዳሉት የተለያዩ የመረጃ ምንጮች ይጠቁማሉ፡፡ ፎቶግራፍ በመሰብሰብና በማደራጀት ልምድ በአውሮፓና በአሜሪካ ቆየት ያለ ታሪክና ለሳይንተናዊ ፍላጐቶቻቸው እንዳዋሏቸው ማወቅ ይቻላል፡፡ በተለይ በአሜሪካ ከ 1750 ጀምሮ በተለያየ መልኩ ሊገልጹ የሚችሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ፎቶግራፎችን በመዛግብት ክምችት ክፍላቸው ውስጥ በማጠራቀም ማንነታቸውንና ታሪካቸውን ጠብቀው ለትውልድ ማስተላለፍ ችለዋል፡፡ ወደ ሀገራችን በምንመጣበት ወቅት የቆዩና ታሪካዊ ፎቶግራፎችን የማሰባሰብ ባህላችን በተለያዩ ፖለቲካዊ ጫናዎችና በጉዳዩ ላይ በቂ ግንዛቤ ያለመያዝና በሌሎችም ችግሮች ምክንያት ደካማ መሆኑ ይታወቃል፡፡

የዚህ የፎቶ ግራፍ ህትመት ዓላማ በኤጀንሲው ከሚገኙ ክምችቶች መካከል ለዚህ ህትመት አስፈላጊ የሆኑትን በመምረጥ ለህትመት አብቅተናቸዋል፡፡ በእነዚህ ፎቶግራፎች ውስጥ ያለውን የሀገራችንን ታሪክ የኋላውን ትዝታ በምናብ እንድናስብና እንድናስታውስ ያደርጉናል፡፡ ወደ ፊት ለመሮጥ ወደ ኋላ መንደርደር መነሻ እንደሆነው ሁሉ ታሪካዊ ፎቶግራፎችም የኋላው ታሪክ ምን እንደሚመስል በማሳየት የቀድሞ አባቶቻችን የሰሩት ስራ ምን እንደሆነና ጠቃሚነቱን በመረዳት አሁን የሚገኘው ትውልድ ግንዛቤ በመውሰድ በዚህ ወቅት ለሚከናወኑ ስራዎች የሞራል ስንቅ በመሆን አዎንታዊ ሚና ይኖራቸዋል፡፡ ፎቶግራፎቹ በሙዚየም ውስጥም በሌሎች ቦታዎች በዐውደ ርዕይነት ለማሳየት ፣ ለተማሪዎች ለትምህርት ማስረጃ ማሳያነት ፣ ለመገናኛ ብዙሀን መረጃ ለሚፈልጉ እንደ መጀመሪያ የመረጃ ምንጭነት ለመጠቀም፣ ለምሁራን ፣ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ ፣ ለአርቲስቶችና ፊልም ለሚሰሩ ድርጅቶች ፣ በተለይ ደግሞ አሁን በህይወት ላሉ የፎቶ ግራፍ ባለቤት ቤተሰቦች እጅግ ጠቃሚ ናቸው፡፡

በዚህም መሠረት የዚህ የፎቶግራፍ ህትመት ይዘት ባህላዊ የኢትዮጵያን የሸንጎ ስርዓት የሚያወሱ ስዕሎችና ፎቶግራፎች፣ በዓፄ ቴዎድሮስ ፣በዓፄ ዮሀንስ ፣ በዓፄ ሚኒሊክ ፣ በዓፄ ሀይለ ስላሴ ፣ በደርግና ፣ በኢህአዴግ ዘመን መንግስታት በተለያዩ ዘርፎች ስመጥር የሆኑ ነገስታት ፣ መኳንንቶች ፣ መሳፍንት፣ የተለያዩ የጦር መሪዎች ፣ ሚኒስትሮች፣ ታዋቂ ግለሰቦችን ፣ የተፈጥሮ መልከአ ምድሮችና የዕምነት ተቋማትን ያቀፈ ነው፡፡ ይህ የፎቶግራፍ ህትመት በተቋሙ ለመጀመሪያ ጊዜ የታተመ ሲሆን በቀጣይ ፈር ቀዳጅ በመሆን በተመሳሳይ ሌሎች ፎቶ ግራፎችን ለማሳተም በጉ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡ በዚህ ዘርፍ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉም ሆነ ለሚማሩ ተማሪዎች ኤጀንሲው እንደ መረጃ ምንጭነት በማገልገል አሁንም ቀዳሚነቱንም ለማረጋገጥ ጥረቱን ይቀጥላል፡፡

## መልካም ንባብና እይታ ይሁንላችሁ፡፡

# ከአጼ ቴዎድሮስ እስከ አጼ ኃይለሥላሴ ስልጣን እስከያዙበት ወቅት ያሉ የፎቶ ግራፎች ስብስብ

ኢትዮጵያ ጥንታዊና ድንቅ የራሷ የሆነ ታሪኮች፣ ባህሎች፣ ቋንቋዎችና ትውፊቶች ያሏት ሰፊ ሀገር ናት፡፡ የኢትዮጵያ በተለያዩ ዘመናት የነገሱ ነገስታት ይብዛም ይነስም ሀገራቸዉን በሁሉም ዘርፎች ለማሳደግ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ በተለይ ሀገራቸዉን ከውጭ ወረራ ጠላት ለመከላከል ያደረጓቸው ጦርነቶች በአብዛኛው ውጤታማና ስኬታማ ነበሩ፡፡ በዚህ የፎቶ ግራፍ ስብስብ ውስጥ አጼ ቴዎድሮስ ከነገሱበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አጼ ኃይለ ስላሴ ድረስ ያሉ ታሪካዊ ፎቶግራፎች ተካተውበታል፡፡

ፎቶግራፎቹ የአጼ ቴዎድሮስ ስእልንና ልጃቸው አለማየሁ በእንግሊዝ ለንደን የተነሳው ፎቶግራፍ ይገኝበታል፡፡ በተጨማሪም ታሪካዊ በሆነው አድዋ ጦርነት ላይ የተሳተፉ የጦር አመራሮች፣ አጼ ዮሀንስ IV ከእንግሊዞች ጋር የተነሱት ፎቶግራፍ፣ እንዲሁም አጼ ሚኒልክ II ንግስና ሲቀበሉ የለበሱትን ልብስ የሚያሳይ ፎቶግራፍና ራስ ተፈሪ መኮንን፣ እንዲሁም የጅማ አባ ጅፋር ፎቶግራፎች ተካተዉበታል፡፡

መልካም እይታ ይሁንላችሁ፡፡



መቅደላ፣ የአጼ ቴዎድሮስ ተራራማዋ
ከተማ 1968.ዓ.ም.



አጼ ቴዎድሮስ 2ኛ ከ1855 ፡ 1968
የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስትና የዘመናዊት ኢትዮጵያ
መስራች



ደጃዝማች ካሳ (አጼ ዮሐንስ 4ኛ) ከተከታዮቻቸው ጋር ከእንግሊዙ ተወካይ ብርጋዲየር ጄኔራል ማሬዉተር እና ከስዊዝ አስተርጓሚው ሙንዚንገር እና በግራ በኩል መሬት ቁጭ ያለው አሞካሪው ካፒቴን ስፒዲ ጋር በ1967 የተነሱት ፎቶግራፍ



የአጼ ቴዎድሮስ ልጅ አለማየሁ በ1968 በጁሊያ ካሜሮን በለንደን እንግሊዝ የተነሳው ፎቶግራፍ



የመቅደላ ቤተክርስቲያን አጼ ቴዎድሮስ የተቀበሩበት
ቦታ በሁለት የእንግሊዝ ወታደሮች ሲጠበቅ



አጼ ዮሐንስ 4ኛ (ከ1872 - 1889)
ከልጃቸው ከራስ አርአያ ስላሴ ጋር



ራስ አሉላ እባነጋ፤የአጼ ዮሐንስ 4ኛ ያጦር መሪ፣ በ 1887 የዶጋሊው ጦርነት አሸናፊና በ1896 የአድዋው ጦርነት ጀኔራል የነበሩ




ራስ መንገሻ ዮሐንስ፤ (1868-1906) የዮሐንስ 4ኛ ልጅና የትግራይ አገረ ገዢ የነበሩ



ንጉስ ተክለ ሐይማኖት የጎጃም ሀገረ ግዛት ንጉስ የነበሩ (1881 - 1901)



ጅማ አባ ጅፋር ሁለተኛ (1861-1932) የአባ ጅፋር 1 (የአባ ጎመል) ልጅ የነበሩ እና የጅማ ንጉስ የነበሩ





አባ ጅፋር 2ኛ ከባለቤታቸው ከገኔ መንጊቲ ጋር
በቤተመንግስታቸው ውስጥ


አጼ ምኒልክ 2ኛ (1855 — 1889) የሸዋ ሀገረ ግዛት
በነበሩበት ወቅት ከጦር አበጋዞቻቸው ጋር የተነሱት
ፎቶግራፍ



አጼ ምኒልክ 2ኛ (ከ1889 - 1913)
የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት ሆነው ንግስና ሲቀበሉ



ንግስት ጣይቱ ብጡል (1851-1918)የንግስና ልብስ
ለብሰው ንግስናን ሲቀበሉ የሚያሳይ ፎቶግራፍ



አጼ ምኒልክ አዲስ አለም ማርያም ቤተክርስቲያን ላይ ሆነው ወደ ታች ሲመለከቱ



ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል (1852-1906) ፤ የሀረሩ ንጉስ፤ የምኒልክ ቀኝ እጅና የኃይለስላሴ አባት



አጼ ምኒልክ ከደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ጋር ሆነው



ወጣት ተፈሪ መኮንን (የወደፊቱ ንጉሰ ነገስት ኃይለስላሴ 1ኛ)፣ከአባቱ ራስ መኮንን ወልደ ሚካኤል ጋር





ራስ መኮንን ወልደሚካኤል ከተከታዮቻቸው ጋር በለንደን በ1901 የንጉስ ኤድዋርድ VII የንግስና ቀን ላይ ሲሳተፉ

አፄ ምኒልክ በዙፋናቸው ላይ



ልጅ መኮንን እንዳልካቸው፣ ልጅ መንገሻ ወሰኔ፣ ፊታውራሪ ነሲቡ ዘአማኑኤል፣ ቀኝ አዝማች ግፋወሰን፣አፈንማቲያስ፣ በጆርጎንድ ዮሴፍ፣ ልጅ አበበ አሰፋው፣ግርማዊት ንግስት ዘውዲቱ፣ ወ/ሮ አፀትለሽ፣ወ/ሮ የሺ፣ ሊቀ መኳስ መኮንን ዋሴቱ፣ ቀኝ አዝማች ወልደገብርኤል ከተፋ፣ ወ/ሮ ትሰሜ አየለ እና አፈ ንጉስ እስጢፋኖስ



ልጅ እያሱ (ከ1913 - 1916) የወሎ ንጉስ የራስ ሚካኤል ልጅና የአፄ ምኒልክ የልጅ ልጅ የነበሩ



ልጅ እያሱ በሰባት አመቱ ከሌሎች ጓደኞቹ ጋር
በእንክብር መዝሙረ ዳዊትን ሲያጠና



የልጅ እያሱና ደጃዝማች ተፈሪ መኮንን ፎቶግራፍ



ራስ ሚካኤል የቀድሞው መሐመድ አሊ (1850-1918)
የወሎ ሀገረ ገዢ የነበሩና የልጅ እያሱ አባት



ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ (1851-1927)
የሚኒልክ የጦር ሚኒስትር፣ በ1896 በአድዋ የጦር
መሪና እስከ 1926 የጦር ሚኒስትር የነበሩ



ደጀአዝማች ባልቻ ሳፎ (1863-1936) ታዋቂ መጠሪያቸው ባልቻ አባ ነፍሶ (የፈረሳቸው ስም) የነበረና በሁሉቱም የፋሽስት ጣልያን ወረራ ላይ ተሳታፊ እና የጦር አዛዥ የነበሩ



ጸሐፊ ትዛዝ ገብረስላሴ ወልደ አረጋ



ራስ ተሰማ ናደው የኢሊባቡር ሀገረ ገዥ የነበሩ፣
የምኒልክ ቤተመንግስት አጋፋሪና የልጅ እያሱ
የሞግዚት አስተዳደር የነበሩ



ታቶ ጋኪ ሳሪቾ የከፋው ታቶ (ንጉስ)

# ቀዳማዊ ንጉሰ ነገስት አጼ ኃይለ ስላሴ ከነገሱበት ጊዜ ጀምሮ የሚገኙ የፎቶግራፍ ስብስቦች ከክምችት ክፍላችን በጥቂቱ

ንጉሰ ነገስት አጼ ኃይለስላሴ ሀገራቸውን ከአርባ አመታት በላይ የመሩ ሲሆን ኢትዮጵያንም በብዙ መልኩ የጠቀሙ ንጉስ ነበሩ:: በሀገራችን ውስጥ ለብዙ ከተሞች መቆርቆርና ማደግ ከፍተኛ ሚና መጫወታቸው ይታወቃል:: በተለይ ደግሞ በዲፕሎማሲው አለም እጅግ የተሳካላቸው ንጉስ እንደነበሩ ይገለጻል:: ለቀድሞው አፍሪካ አንድነት ድርጅት መመስረት ከሌሎች አፍሪካ መሪዎች፣ ከነ ኳሚ ንክሩማ፣ ጆሞ ኬንያታና ጁሊየስ ኔሬሬ ጋር ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል:: ኢትዮጵያን እ/ኤ/አ በ1923 የሊግ ኦፍ ኔሽንስ (league of nations) አባል ከማድረጋቸውም ባሻገር የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (UNO) አባል እንድትሆን አድርገዋል:: ከሌሎች አፍሪካ ሀገሮች በተለየ ኢትዮጵያ ከቅኝ ግዛት እራሷን የተከላከለች በመሆኗ የነጻነት ምልክትና ተምሳሌት ሆና እንድትቆጠር የሁሉም ኢትዮጵያዊ ውጤት ቢሆንም የመሪነት ሚና በመጫወት የማይናቅ አስተዋጽዎ ነበራቸው::

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የሚለው ስሟ በአለም መድረኮችና ጉባኤዎች የላቀ ክብር የሚሰጣትና ዜጎቿም በሌሎች ሃገሮች ዜጎች ከፍ ያለ ክብር የሚሰጣቸው ህዝቦች እንደነበሩ የተለያዩ ጽሑፎች ያወሳሉ:: በዚህ ታሪካዊ የፎቶግራፍ ስብስብ አጼ ኃይለስላሴ በተለያዩ ጊዜያትና ምክንያቶች የተነሷቸው ፎቶግራፎች፣ ከመንግሳቸው በፊት ከልዑካን ቡድኑ ጋር በመሆን በአውሮፓ ጉብኝት ሲያደርጉ፣ የአባይ ወንዝ ለኤሌክትሪክ አገልግሎት መዋል እንደሚችል ሲያዩ፣ የካቲት 12 አደባባይ ተብሎ የተሰየመውን ሐውልት መርቀው ሲከፍቱ፣ ከውጪ ሃገር ወደሀገራቸው በሱዳን በኩል አድርገው በጎጃም ሲገቡ የሚያሳይ ፎቶግራፍና ሌሎችም ፎቶግራፎች ተካተዋል::

መልካም እይታ ይሁንላችሁ::





ቀዳማዊ ግርማዊ ኃይለስላሴ በቤተመጽሐፍት ክፍላቸው ውስጥ ሲያነቡ

ግርማዊ ንጉሰ ነገስት ከምዕራብ ጀርመን ፌድራል መንግስት በዕርዳታ ለፖሊስ ሠራዊት ትራፊክ ሥራ አገልግሎት እንዲውል የተሰጡትን ዕቃዎች ሲጎበኙ





ራስ ተፈሪ መኮንንና የልዑካን ቡድኑ በአውሮፓ ጉብኝት ወቅት የቫርሳይለስ ቤተመንግስትን ሲጎበኙ (1924)

ግርማዊ ንጉሰ ነገስት የአባይ ወንዝን ለኤሌክትሪክ አገልግሎት መዋሉን ሲመለከቱ





ግርማዊ ንጉሠነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በ1960ዎቹ በተካሄደው የኮንጎ ጦርነት ጃንሆይ ሜዳ ተገኝተው ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኮንጎ ግዳጅን ፈጽሞ ለተመለሰው ሠራዊት የኒሻን ሽልማት ከሰጡ በኋላ መሪ ቃል ሲናገር

ግርማዊ ጃንሆይ የካቲት 12 አደባባይ ተብሎ የተሰየመውን አደባባይና ሐውልት መርቀው ሲከፍቱ





በ1928 የኢጣልያ ወረራ በፊት የተነሣ ቀ.አጼኃይለስላሴ በስተግራ የሚታዩት የሀረሩ መስፍን ልጃቸው መኮንን ሲሆኑ ከአጼኃይለስላሴ በስተጀርባ በስተቀኝ የሚታዩት የአብሲኒያው ራስ ጉቲን አባ ሻና ናቸው።

ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለስላሴ ከኢጣልያ ጦርነት በኋላ ከእንግሊዝ መንግሥት ጋር ውል ሲዋዋሉ (1942)





ከ1941 የነጻነት ድል በኋላ በገነተ ልኡል ቤተመንግስት ለግርማዊ ንጉሰ ነገስት፣ ለአቡነባሲሊዎስ፣ ብርጋዴር ጀኔራል ሳንፎርድና ሌሎችም መኳንንት በተገኙበት የነጻነት ታጋዮች ፉከራና ቀረርቶ ሲያቀርቡ የሚያሳይ

ግርማዊ ንጉሰ ነገስት ከሸሸት ወደ ሀገር ቤት በሱዳን በኩል ወደ ጎጃም የተደረገ ጉዞ ፎቶግራፎች ከግራ ወደቀኝ ራስ ቤትወደድ መኮንን እንዳልካቸው፣ አባህናና ኀለማየሁ ናቸው።





ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ በህዝብ በዓል ላይ ንግግር ሲያደርጉ ፎቶግራፉ ከግራ ወደቀኝ ግርማዊ ነታቸው፣ ደጃዝማች መንገሻ ይልማ፣ አቶ ዳባ ብሩና ደጃዝማች አያፍርሰው(ራስ)

ከግራ ወደቀኝ ራስ ጌታቸው አባተ፣ ራስ ብሩ ወልደገብርኤል፣ ልዑል አልጋ ወራሽ አስፋወሰን፣ ብላቴን ጌታ ህሩይ ወልደ ሥላሴ፣ ራስ ከበደ መንገሻ፣ ቢት ወደድ ወልደጻድቅ፣ ቢትወደድ ወልደገብርኤልና ኢጋፋሪ ከልክሉ ናቸው።





የኢትዮጵያ ልዑካን ቡድን በጋና አክራ
(1960ዎቹ መባቻ)

የተለያዩ የአፍሪካ መሪዎች በታሪካዊው ኮንፈረንስ
ላይ የመዝግግያዉ ቀን የተነሱት የጋራ ፎቶግራፍ
(1963)



የአፍሪካ መሪዎች በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ምስረታ ወቅት



ሚስተር ኮፊባኮ የጋና የመረጃና መገናኛ ሚኒስትር በጋና አክራ የአባል ሀገራት የተሳተፉበትን አውደ ርዕይ ሲከፍቱ





የኢትዮጵያ ተወካይ ከላይቤሪያው ፕሬዘዳንት ቱብማን ጋር ሰላምታ ሲለዋወጡ

የኢትዮጵያ ተወካይ የሱዳኑን ልኡካን ቡድን መሪ መሐመድ አህመድ ሙሐጀብን ሲቀበሉ





ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ
በኒዎርክ በጀማል አብዱል ናስር አቀባበል ሲደረግለት

የሊቢያዊ መሪ መሀመድ ጋዳፊና የሱማሊያው መሪ
ዚያድባሬ



# በቀዳማዊ ንጉሰ ነገስት አጼ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት በፋሽት ኢጣሊያን ወረራ ወቅት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉ አርበኞች የፎቶግራፍ ስብስቦች ከክምችት ክፍላችን በጥቂቱ

ኢትዮጵያ የአድዋን ጦርነት ድል ካደረገች ከአርባ አመታት በኋላ ፋሺስት ኢጣሊያ ቂም ቋጥሮ እንደገና በ1928 ዓ.ም ወረራ በማድረግ በመላ ሀገሪቱ በሰዎች ላይ፣ በንብረትና በእንስሳት ላይ ከፍተኛ ውድመትና ቀውስ ፈጥሯል:: ይህም ኢትዮጵያውያንን ለከፍተኛ ቁጣና ወኔ ስለዳረገ ሀገራቸውን ከወራሪ ጠላት ለመከላከል በተለያዩ የሀገሪቱ አቅጣጫዎች በዱር በገደሉ በመሰማራት ፋሺስት ኢጣሊያንን መዋጋት ጀመሩ:: በዚህ ሂደት ዉስጥም በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞው ገነተ ልዑል እየተባለ በሚጠራው ቤተመንግስት ዉስጥ አብረሃም ደቦጭና ሞገስ አስገዶም የተባሉ ወጣቶች በወቅቱ አዲስ አበባን በሚያስተዳድረው ማርሻል ግራዚያኒ ላይ የመግደል ሙከራ አድርገው ከፍተኛ የመቁሰል አደጋ ካደረሱበት በኋላ በኢጣሊያኖች ላይ ቁጣን በመቀስቀሱ ለጦርነት በተከለከለ መርዛማ ጋዝና ከባድ የጦር መሳሪያዎችን በመጠቀም ብዙ የሳር ጎጆዎችን በማቃጠል በህዝቡ ላይም ዘግናኝ ጭፍጨፋ በመፈፀም በአንድ ቀን ብቻ ከሰላሳ ሺህ በላይ ሰዎች ገድለዋል::

ጀግኖች አርበኞች የጠላት ወረራን ለመመከት ለአምስት አመታት እልህ አስጨራሽ ትግልና የህይወት መስዋዕትነት ከፍለው ሀገራቸው መልሳ ነጻነቷን እንድትጎናጸፍ አድርገዋል:: በመቀጠልም ንጉሰ ነገስት አጼ ኃይለ ስላሴ ከእንግሊዝ ሀገር በመመለስ በእንግሊዝ መንግስት ትብብር እንደገና ንግስናቸውን ማስቀጠል ችለዋል:: አሁን የሚገኘው ትውልድ ከጥንታዊ ጀግኖች አርበኞ የሀገር ፍቅር ስሜትና ለሀገር የሚከፈለውን መስዋዕትነትና ቁርጠኝነት እንደ ተሞክሮ በመውሰድ አሁን ሀገራችንን በሁሉም ዘርፍ እየተፈታተኑ የሚገኙ ችግሮችን ለመቅረፍ በተሰጠን መከሊትና በተሰማራንባቸው የሙያ መስኮች ውጤታማ በመሆን የበኩላችንን አስተዋፅዎ ማድረግ ይጠበቅብናል::

## መልካም እይታ ይሁንላችሁ::



ራስ አሞራው ውብነህ በምዕራብ ጎንደር አካባቢ በፀረ ፋሽስት ላይ ተጋድሎ ያደረጉ የኢትዮጵያ አርበኛ



ራስ አበበ አረጋይ (1903-1960)
በመንዝና በሸዋ አካባቢ በፀረ-ፋሽስት ላይ ተጋድሎ ያደረጉ የኢትዮጵያ አርበኛ



ሻምበል አበበ ቢቂላ የክብር ዘበኛ በቤተመንግስት ውስጥ በነበሩበት ወቅት



ደጅ አዝማች አበበ ሽንቁጥ የፀረ ፋሽስት ኢጣሊያ ተጋድሎ በመራቢቴና አካባቢው ታላቅ ተጋድሎ ያደረገ ጀግና



ልጅ ሐይለማሪያም ማሞ (1904- 1938)
በፋሽስት ወረራ ጊዜ ቆራጥ ጀግና እና አርበኞች
በማስተባበር የታወቁ ነበሩ



አቡነ ጴጥሮስ (1892 - 1936) የወሎ ሊቀ ጳጳስ፣
የፋሽስት ወረራና እልቂት በመቃወማቸው በግፍ
ተገድለው ሰማዕት የሆኑ የሀይማኖት አባት እና አርበኛ



ራስ ካሳ ሀይሉ ዳርጌ(1881- 1956)
ከፋሽስት ጋር በተዝቤን ግንባር ላይ የተዋጉና ከነፃነት በኋላም የአፄ ኃይለስላሴ ከፍተኛ ባለስልጣን የነበሩ



እናት አርበኛ ወ/ሮ ልኪለሽ በያን
በፋሽስት ወረራ ላይ ጠንክራ ተጋድሎ ያደረጉ እናት አርበኛ



ብርጋዴር ጀኔራል መንግስቱ ነዋይ(1916- 1961)
የ1953ቱን መፈንቅለ መንግስት ያስተባበሩና በሙከራው ህይወታችውን ያጡ



ግርማሜ ንዋይ(1924- 1960)
የወላይታና የጅጅጋ አስተዳዳሪ የ1953 መፈንቅለ መንግስት አስተባባሪና በሙከራው የተሳተፉ



ጀኔራል መርዕድ መንገሻ (1912-1966) በቀዳማዊ ኃ/ስላሴ ዘመነ መንግስት የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩ



ኮሎኔል አብዲሳ አጋ፤
በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጪ የፋሽስት ኢጣሊያኖን ያርበደበዱ ሀገር ወዳድ አርበኛ የነበሩ





ፊት አውራሪ ገረሱ ዱኪ (ደጃአዝማች)
በደቡብ ምዕራብ ሸዋ የፋሽስት ኢጣሊያንን ጦር
ያርበደበደ የኢትዮጵያ አርበኛ የነበሩ



ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ 5000 የኢትዮጵያ አርበኞችን
በመምራት በጅማ አባ ጅፋር የጣሊያን ጦርን
ለማጥቃት በጉዞ ሳሉ በ1935



የቢቸናው ጀግና ደጃዝማች በላይ ዘለቀ(1912-1945) አባኮስትር ፋሽስት ኢጣሊያንን በጎጃም አከባቢ በአርበኝነት ያርበደበደ ጀግና



ጀኔራል ጃገማ ኬሎ (1913-2009) ግንቦት 22 ቀን 1933 ዓ.ም.በአርበኝነት ጊዜው ካጎፈረው ጸጉሩ ጋር ለመታሰቢያነት የተነሳው ፎቶ



የኮሪያ ዘማቾች ቃኘው ሻለቃ ክፍለ ጦር በኮሪያ ሀገር በውጊያ ላይ ሳሉ (1950-53)



እናት አርበኛ ሸዋረገድ ገድሌ(1878-1942) ከኢጣሊያን ወረራ በፊት የኢትዮጵያ ሴቶች ማህበር ፕሬዝዳንት እና የእኩሪ ገድል ባለቤት ናቸው

# በደርግ ዘመነ መንግስት የነበሩ የፎቶግራፍ ስብስቦች በጥቂቱ ከክምችት ክፍላችን

ኢትዮጵያን ከአርባ አመታት በላይ በንጉሰነት ሲገዙ የነበሩት ቀዳማዊ አጼ ኃይለስላሴን 1967 ዓ.ም በደርግ መፈንቅለ መንግስት ተደርገባቸው ስልጣናቸውን እንዳጡ ይታወቃል፡፡ ከዛም በኋላ ደርግ ሀገሪቷን ለአስራ ሰባት አመት ከመግዛቱም ባለፈ የተለያዩ መሰረተ ልማቶችን ማለትም የተለያዩ ፋብሪካዎችን፣ ማሰልጠኛ ተቋማትን፣ የግብርናና የእደጥበብ ድርጅቶችን በመክፈት ለሀገሪቱ ዜጎች የስራ እድል ከመፍጠርም ባሻገር ለሀገር ኢኮኖሚ ቀጥተኛ አስተዋጽዎ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡ በመቀጠል የምትመለከቷቸው ፎቶግራፎች ጓድ (ኮሎኔል) መንግስቱ ኃይለማርያም እንዲሁም ሌሎች ባለስልጣናት በተለያየ ጊዜ የተነሷቸው ፎቶ ግራፎች ሲሆኑ፣ ደርግ የድል በዐሉን በአብዮት አደባባይ በየአመቱ መስከረም 2 ሲያከብር የሚያሳይ የፎቶግራፍ ምስል፤ ጓድ መንግስቱ ኃ/ማርያም በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍለ ሃገሮች በመሄድ የተለያየ ገጽታ ወይም ፋይዳ ያላቸውን ፋብሪካዎችና ሰርቶ ማሳያዎችን ሲጎበኙ እንዲሁም በደርግ ዘመነ መንግስት የነበሩ የተለያዩ ሚኒስቴር መስርያ ቤት ሀላፊዎች የተነሷቸው ፎቶግራፎች በኤጀንሲው ክምችት ክፍሎች ይገኛሉ፡፡

ተቋማችን እነዚህን ፎቶግራፎች በቂ ጥበቃና እንክብካቤ በማድረግ ለሚቀጥለው ትውልድ ከማስተላለፉም ባሻገር ማንኛዉንም አይነት ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ ባለሙያዎች፣ ተማሪዎች፣ ምሁራን በተጨማሪም የሃገራቸውን ታሪክ ማወቅ ለሚፈልጉ ወገኖች አገልግሎቱን እንደምንሰጥ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡

መልካም እይታ ይሁንላችሁ፡፡



ኮለኔል መንግስቱ ኃይለ ማሪያም 1981 ዓ.ም.



የደርግ መንግስት የድል በዓል አከባበር በአብዮት አደባባይ እንዲህ ነበር





ጓድ መንግስቱ ሀ/ማርያም በፍንጫ መብራት ሃይል ተገኝተው ሲጎበኙ

ጓድ መንግስቱ ኃ/ማርያም በባህርዳር መግለጫ ሲደረግላቸው



ኮሎኔል አበበ በላይነህ ለዘማቾች ንግግር ሲያደርጉ



አቶ ጎሹ ወልዴ በደርግ ዘመን መንግስት የትምህርት ሚኒስቴርና በኋላም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩ



ዶክተር አሻግሬ ይገለጡ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር
የነበሩ



ዶክተር ጄኔራል ግዛዉ ፀሐይ የጤና ጥበቃ ሚ/ር
በደርግ ዘመነ መንግስት



ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም የሀሳዕና የእደ ጥበብ ዉጤቶችን ሲጎበኙ



ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም በደሌ ቢራ ፋብሪካን በመጎብኘት ላይ እያሉ



ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም የከፋን የቡና ልማት ፕሮጀክትን ሲጎበኙ



ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም በደብረ ታቦር አውራጃ በመገኘት የሸማቾች አምራቾች ህብረት ስራ ማህበር ሲጎበኙ





ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም በሐረር እርሻ ሰብል ድርጅት በመገኘት ጉብኝት ሲያደርጉ


ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም የነቀምት ሆስፒታልን ሲጎበኙ



ዶክተር ያየህ ይራድ ቅጣው በደርግ ዘመን መንግስት
የትምህርት ሚኒስትር የነበሩ



የደርግ ወታደሮች ፎቶግራፍ በ1980ዎቹ



ዶክተር (ፕሮፌሰር) ላጲሶ ዴሌቦ
የኢትዮጵያ የታሪክ ሙሁርና ተመራማሪ



የኢትዮጵያ ሰራዊት በሱማሊያ የተወረረውን ሀገሩን
ዳር ድንበር ለማስከበር ወደ ኦጋዴን ሲዘምት

# የኢህአዴግ መንግስት የቀድሞ ባለስልጣናት ፎቶግራፎች ከአርካይቭ ክምችት ክፍሎች ውስጥ

ኢህአዴግ ኢትዮጵያን በ1983 ዓ.ም. ከተቆጣጠረ በኋላ በሀገሪቱ አዲስ የፖለቲካ ስርአት እንዲሁም የህዝቦችን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያረጋግጥ ህገ-መንግስት ለመጀመርያ ጊዜ ማስተዋወቅ ተችሏል፡፡ የፎቶ ግራፍ ስብስቦች የአንድን ሀገር ሁለንተናዊ ታሪክ ጠብቆ በማቆየት ያላቸው አስተዋጽዎ ጥያቄ ዉስጥ የሚገባ አይደለም፡፡ በተለይ ደግሞ በሃገሪቱ ታሪክ የትምህርት ዘርፍ ካሪኩለም ውስጥ ለማካተት መነሻ በመሆን ቀጥተኛ አስተዋጽዎ ይኖራቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የፎቶ አርካይቭ መረጃዎችን ለተለያየ አላማ ለሚፈልጉ አካላት፣ እንዲሁም በዘርፉ ጥናትና ምርምር ለሚያደርጉ ተቋማትና ግለሰቦች የጎላ ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡ ከታች የምታይዋቸው ፎቶግራፎች በኢህአዴግ ዘመን መንግስት የነበሩ ባለስልጣናት፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚንስትር አቶ መለስ ዜናዊ፣ የቀድሞ ፕሬዝደንት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ፣ እንዲሁም የወቅቱ ጠቅላይ ሚንስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የኤጀንሲውን ጥንታዊ ስጽሑፍ ቅርሶችን ሲጎበኙ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ ተካቶበታል፡፡

መልካም እይታ ይሁንላችሁ፡፡






የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስተር ክቡር መለስ ዜናዊ በትጥቅ ትግል መቅት ከትግል አጋሮቹ ጋር

የኢህአዴግ የጦር ታጋዮች በ1980ዓ.ም አካባቢ



አቶ መለስ ዜናዊ የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩ (1987-2004)



ዶክተር ነጋሶ ጊዳዳ የኢፌድሪ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር፣ ማስታወቂያ ሚኒስትርና የኢፌድሪ ፕሬዘዳንት የነበሩ



አቶ ስዩም መስፍን የኢፌድሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር የነበሩ (1991-2010)



ዶክተር አዳነች ኪዳነ ማሪያም የጤና ጥበቃ ሚኒስትር



ዶክተር አዜብ ታምራት የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር የነበሩ



ወ/ሮ ገነት ዘውዴ የኢፌድሪ ትምህርት ሚኒስቴር የነበሩ



ዶክተር አደም ኢብራሂም የኢፌድሪ ጤና ጥበቃ ሚኒስትር የነበሩ



አቶ ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ የኢፌድሪ ፕሬዘዳንት የነበሩ





የኢፌድሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማሪያም ደሳለኝና ሌሎች ሚኒስተሮች በኤጀንሲው ከሚገኙ ጥንታዊ የስነፅሑፍ ሀብቶችን ሲጎበኙ

በ1983ዓ.ም የሌኒን ሐውልት ከወደቀ በኃላ የሚያሳይ ፎቶ

# የተለያዩ ፎግራፎች ከመዛግብት የክምችት ክፍል ውስጥ ከሚገኙ በጥቂቱ



የቀድሞው ወመዘክር ሕንፃ፣ የአሁኑ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻሕፍት ኤጀንሲ በ1936 ዓ.ም በግርማዊ ኃይለስላሴ የመጻህፍት ድጋፍ የተመሰረተ



የብራና መጽሕፍት በደብረ ሊባኖስ በ1939 የተነሳ ፎቶግራፍ



በእንክባር፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን



ውሪያማሩ፣ በጋንቤላ የአከባቢው መሪ፣ ከቤተሰቦቹ.



የ20ኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያን ታሪክ አዋቂ
አለቃ አስሜ ከቤተሰቦቹ ጋር



ከግራ ወደ ቀኝ ደስተኞቹ
ሃጎስ፣ደስታ፣መብራቱና ተስፋዬ





ተንቀሳቃሽ የሕዝብ ቤተመጽሐፍት በኢትዮጵያ

የቅዱስ ጊዮርጊስ ካቴድራል ቤተክርስቲያን፣
አዲስ አበባ በ1917 ዓ.ም



ካርሎኮንቲሮሲኒ (1872-1949)
የኢትዮጵያ ታሪክ ፀሐፊና የጣልያን ተወላጅ የነበረ



ጀምስብሩስ የጥቁር አባይ መነሻን ያገኘ የስኮትላንድ
ተወላጅ





መሐመድ አሊ ህንዳዊው ነጋዴ በኢትዮጵያና
የመጀመሪያው የግል መኪና ባለቤት

ከቀኝ ወደ ግራ ሐይሌ ፊዳና ነገደ ጎበዜ በአውሮፓ
የተነሱት ፎቶ 1970ዎቹ





ጀግናው አትሌት ሺ አለቃ አበበ ቢቂላ የቤተ መንግስት ጠባቂ በነበረበት ጊዜ የተነሳው ፎቶግራፍ

የሸንኮራው ነጋዴ በአዲስ አበባ ጎዳና ላይ በ 1970ዎቹ





የጎንደር ባህላዊ የግብይት ስርዓት በ1930ዎቹ

ታዋቂው የኦሮምኛ ዘፋኝ ዶ/ር አርቲስት አሊ ቢራ

# በክምችት ክፍሎች ውስጥ ከሚገኙ የስዕል ስብስቦች በጥቂቱ

ብሄራዊ ቤተመዛግብትና ቤተመጻህፍት ኤጀንሲ ስር የሚገኙ በተለያዩ ደራሲያንና ሰአሊያን የተዘጋጁ ስእሎችና ፎቶ ግራፎች የተካተቱበት ሲሆን በተለይ ደግሞ የአፋርና የሶማሌ ብሄረሰቦች በወቅቱ የነበሩ የአለባበስ፣ የጦር መሳርያዎች፣ ባህላዊ ሸንጎዎች እንዲሁም በሸዋ ክፍለ ሀገር የእንግሊዞች መኖርያ ቤትና የአንኮላ ቤተመንግስት በእንግሊዞች ሰአሊያን ከ1940 ጀምሮ የተሳሉ ናቸው።

ከዚህ በተጨማሪም በሀገራችን እውቅ ሠዐሊ በሆኑት በሜትር አርቴስት የአለም ሎሪት አፈወርቅ ተክሌ አለምን ያስደመሙና የተለያዩ ሽልማቶችን ያስገኙላቸው ሥዕሎች ቀርበዋል። እነዚህ ሥዕሎች የኢትዮጵያ ቱባ ባዕሎችን የሚገልጹ ሥዕሎቻቸው በጥቂቱ ተዳሰዋል ።


መልካም እይታ ይሁንላችሁ።





የኢሳ ሶማሌ ባህላዊ አለባበስ ከ1943-1947 እ.አ.አ
በዊሊያን ሲ. ሐሪስንና ሔርማርቲን ብራኑፎዝ
የተሳለ

በአፋር የሚገኙ የደናክል ጀግኖች ባህላዊ አለባበስ





የሶማሌ ባህላዊ ምክር ቤት (ስብሰባ)

ባህላዊ የፍትህ ስርዓት በኢትዮጵያ





የእንግሊዞች መኖሪያ ቤት በአንኮበር ( ሸዋ)

የፍትህ ምክር ቤት በሸዋ አንጎላላ ቤተመንግስት






የታጁራ አገረ ገዥ (sultan of Tajura)


የኦሮሞ ሴቶች ባህላዊ አለባበስ



የኢትዮጵያን ውስጣዊ የቤት አቀማመጥ
የሚገልጽ ሥዕል



ወታደራዊ ዘመቻ በሸዋ አንጎላላ



ከድል መልስ ሸዋ በአንጉላላ



የሸዋው ንጉስ ሳህለ ስላሴ የንጉስ ቀዳማዊ
ምኒሊክ አያት ሥዕል



ንጉስ ሀይለ መለኮት ሣህለ ስለሴ የሸዋ ንጉስ
( የአፄ ምኒሊክ አባት)



አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ



ሜትር አርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ከንጉስ ነገስቱ የክብር ሽልማት ሲቀበሉ (ፎቶግራፍ)



ሜትር አርቲስት የአለም ሎሬት አፈወርቅ ተክሌ በ1962 ዓ.ም. የተነሱት ፎቶ ግራፍ



የኢትዮጵያዊት እናት ስዕል የሚገልጽ በ1963 ዓ.ም.



የአድዋ ሴት ስዕል በ1965 ዓ.ም. ( በአፈወርቅ ተክሌ የተሳለ)



የመስቀል አበባ በ1963 ዓ.ም. ( በአርቲስት አፈወርቅ ተክሌ የተሳለ)



የመጨረሻው ፍርድ 1958 ዓ.ም. ( በአርቲስት አፈወርቅ ተክሌ ተሳለ )

## በዩኔስኮ የተመዘገቡ 12ቱ የስነፅሁፍ ቅርሶች በኤጀንሲው የክምችት ክፍል ውስጥ የሚገኙ የብራና መጽሕፍት



የሐዋርያዉ ቅዱስ ጳዉሎስ መልእክት (በ15ኛዉ ክፍለ ዘመን የተፃፈ)
St.Paul's Epstiles 15th Century)



አርባዕቱ ወንጌል ቅዱስ (በ14ኛዉ ክፍለ ዘመን የተፃፈ)
The Four Gosplels /Bible, New Testament/ (14th Century)



መጽሐፈ ግብረ ሕማማት (በ15ኛው ክፍለ ዘመን)
Homily of the Passion of our Lord and Services for Passion week (15th century)



መጽሐፈ ሄኖክ /በ15ኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈ/
Book of Enoch (15th century)



መዝሙረ ዳዊት በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፈ
Psalterium Davids 16th Century



የዳግማዊ አጼ ምኒልክ ታሪክ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፈ
History of Menelik II 19th Century



መጽሐፈ ቅዳሴ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፈ
Anaphora 17th Century



መጽሐፈ ፍትሐ ነገሥት በ19 መቶ ክፍለ ዘመን
Fetha Negest /NomoCanon/ 19th Century




ከዳግማዊ አፄ ምኒልክ ለሞስኮዉ
ንጉስ ኒኮላኣስ ቄሣር ሁለተኛ የጻፉት ደብዳቤ
19ኛዉ መቶ ክፍለ ዘመን




የሸዋዉ ንጉስ ሣህለ ስላሴ ለእንግሊዝ ንግስት የፃፉት ደብዳቤ
Letter of King Sahle Selassie of Shoa to the Queen of Britain



አጼ ቴዎድሮስ ለእንግሊዝ ንግሥት ቪክቶሪያ የጻፉት ደብዳቤ (19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን)
Letter of king Theodros to Queen Victoria of Britain (19th Century)



መጽሐፈ ባሕረ ሐሳብ (የኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር) በ1755ዓ.ም



መጽሐፍ ብሉይ ኪዳን
(በ250 የበግ ቆዳ የተዘጋጀ)





